# የጉምሩክ ትራንዚት አፈፃፀም

## መመሪያ ቁጥር168/2012

የካቲት 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2
በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Customs Commission
Documentation No.1

# <u>የጉምሩክ ትራንዚት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር168/2012</u>

የገቢ፣ የወጪ፣ የተላላፊ እና የሀገር ውስጥ ትራንዚት ዕቃዎች መተላለፊያ መስመር ለመወሰን ቀላል፤ ቀልጣፋና ወጥነት ያለው የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ከገቢ፣ ከወጪ እና ተላላፊ የንግድ ዕቃዎች በመተላለፊያ መንገዶች ላይ ያሉ ተደጋጋሚ ፍተሻዎችን በመቀነስ እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የጭነት ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት የንግድ እንቅስቃሴውን ማሳለጥ በማስፈለጉ፤

ሚኒስቴሩ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 180(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን የአፈጻጸም መመሪያ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>
## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ "የጉምሩክ ትራንዚትአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር168/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

   1/ "የትራንዚት ዕቃ" ማለት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ሳይጠናቀቅ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆኖ ከአንድ የጉምሩክ ጣቢያ ወደ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ በተፈቀደ መሥመር የሚጓጓዝ ዕቃ ሲሆን እንዳስፈላጊነቱከጉምሩክ ጣቢያ ውጭ በተፈቀደ ቦታ የሚጫንና የሚራገፍ ዕቃን ይጨምራል፡፡

   2/ "የጉምሩክ ትራንዚት አፈፃፀም" ማለት የትራንዚት ዕቃ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆኖ ከጉምሩክ መነሻ ጣቢያ እስከ መድረሻ ጣቢያ ወይም ወደተፈቀደ ቦታ የሚተላለፍበት ሂደት ነው፡፡

   3/ "የትራንዚት መነሻ ቦታ"ማለት የጉምሩክ ትራንዚት የሚጀምርበት የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ወይም በጉምሩክ የተፈቀደ ቦታ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በጎረቤት ሀገራት ያሉ የኮሚሽኑ ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶችንም ይጨምራል፡፡



Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenue
Records & Documentation No. 2

4/ "የትራንዚት ማጠናቀቂያ ቦታ" ማለት የጉምሩክ ትራንዚት የሚጠናቅበት የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤትወይም ጣቢያ ወይም በጉምሩክ የተፈቀደ ቦታ ነው።

5/ "መግቢያ በር" ማለት የትራንዚት ዕቃ ወደ ጉምሩክ ክልል ተጓጉዞ የሚገባበት በር ነው።

6/ "የጉምሩክ ማሸጊያ" ማለት በኮሚሽኑ እውቅና የተሰጠው የትራንዚት ዕቃ ደህንነት ለማስጠበቅ የሚረዳ የዕቃ መያዣወይም የጭነት ማጓጓዣ ማሸጊያ ነው።

7/ "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት በማጓጓዣው ላይ የደረሰ ብልሽት ወይም አደጋ ወይም በአጓጓዡ ላይ የደረሰ ከባድ ህመም ወይም የመንገድ መዘጋት ወይም ክልከላ ወይም በፀጥታ ምክንያት የተፈጠረ የጉዞ ወይም ተዛማጅ ሌላ ማንኛውም አስገዳጅ ሁኔታ ማለት ነው።

8/ "ከአቅም በላይ ለሆነ ምክንያት የሚቀርብ ማስረጃ" ማለት በጉምሩክ ትራንዚት አፈፃፀም ወቅት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ የገጠመው አጓጓዥ ሁኔታውን በአቅራቢያው ለሚገኝ የኮሚሽኑ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ወይም ጣቢያ ወይም ህግ አስከባሪ ወይም መስተዳደርወይም አግባብ ያለው አካል አሳውቆ ከዚሁ አካል የተሰጠ የጽሑፍ ማረጋገጫ ነው።

9/ "ፓትሮሊንግ" ማለት የትራንዚት ዕቃ ከትራንዚት መተላለፊያ መሥመር ውጭ ሲንቀሳቀስ ወይም ማጓጓዣው ጉዞውን ገትቶ ዕቃ ሲያራግፍ ወይም ሲጭን ወይምሌላ አጠራጣሪ ሁኔታ ሲኖር የጉምሩክ ቁጥጥር ግብረ-ሃይል ወደ ቦታው በመንቀሳቀስ ቁጥጥር የሚያደርግበት ሂደት ነው።

10/ "ኮሚሽን" ማለት የጉምሩክ ኮሚሽንነው።

13/ "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለው)ነው።

14/ በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸው ሌሎች ቃላትበአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በትራንዚት ዕቃ እናበማጓጓዣው እንዲሁምበአጓጓዡ እና በአስተላላፊው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን *1*
Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1
በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

## ክፍል ሁለት
## የጉምሩክ ትራንዚት አፈጻጸም

### ምዕራፍ አንድ
### ቅድመ ሁኔታ

4. **መርህ**

1/ ማንኛውም ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ወይም ከሀገር የሚወጣ ዕቃ ወይም አገር አቋርጦ ወደ ሌላ አገር የሚተላለፍ ዕቃ በቅድሚያ የጉምሩክ ትራንዚት ፈቃድ ማግኘት አለበት፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በመልቲ-ሞዳል ትራንስፖርት ለሚጓጓዝ ዕቃ የጉምሩክ ትራንዚት ፈቃድ ላያስፈልግ ይችላል፤

5. **የገቢ ዕቃ ትራንዚት**

1/ በዩኒ ሞዳል ትራንስፖርትተጓጉዞ ወደ ሀገር ለሚገባ ዕቃ በአገር ውስጥ ካሉ የጉምሩክ ጽ/ቤቶችየትራንዚት ፈቃድ ለማግኘትአስመጪው ወይም ወኪሉ የሚከተሉትን ማቅረብ አለበት፤

ሀ) የትራንዚት ዲክላራሲዮን (IM8) ፣

ለ) ለቀረጥና ታክስ ክፍያ ተመጣጣኝ የሆነ ዋስትና ወይም የቀረጥ ነፃ መብት ደብዳቤ፣

ሐ) የማጓጓገር ሰነድ፣

መ) ዕቃው በኮንቴነር የሚጓጓዝ ከሆነ የኮንቴነር ዋስትና

2/ በዩኒ ሞዳል ትራንስፖርት ተጓጉዞ ወደ ሀገር ለሚገባ ዕቃ በጎረቤት አገር ከሚገኝ የጉምሩክ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ወይም እንደሁኔታው በጎረቤት አገር ጉምሩክ የትራንዚት ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፤

3/ በጎረቤት አገር ከሚገኝ የጉምሩክ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ለሚሰጥ የትራንዚት ፈቃድ አስመጪው ወይም ወኪሉ የሚከተሉትን ማቅረብ አለበት፤

ሀ) ኮሜርሻል ኢንቮይስ፣

ለ) የትራንዚት ዲክላራሲዮን (IM8)

ሐ) የማጓጓገር ሰነድ፣

መ) ለቀረጥና ታክስ ክፍያ ተመጣጣኝ የሆነ ዋስትና ወይም የቀረጥ ነፃ መብት ደብዳቤ፣

Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

4/ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት በትራንዚት ተጓጉዘው ወደ ሀገር ለሚገቡ ዕቃዎችየመልቲ-ሞዳል ትራንስፖርት ኦፕሬተሩ አጠቃላይ ዋስታና ለጉምሩክ ማስያዝ አለበት፡፡

5/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እንደተጠበቀ ሆኖበጎረቤት አገር ጉምሩክ የተሰጠ የትራንዚት ዲክላራሲዮን (IM8) እና የመንገድ ወረቀት (T1) በመግቢያ በር ለሚገኝ ጉምሩክ መቅረብ አለበት፡፡

6. <u>የተላላፊ ዕቃ ትራንዚት</u>

1/ አገር አቋርጦ ወደ ሌላ አገር የሚተላለፍ የትራንዚት ዕቃ ፈቃድ ለማግኘት አስመጪው ወይም ወኪሉ የሚከተሉትን ማቅረብ አለበት፤

ሀ) ዋስትና፣

ለ) ትራንዚት ዲክለሬሽን (IM8) ፣

ሐ) ኮሜርሻል ኢንቮይስ፣

መ) የማጓጓዣ ሰነድ፣

ሠ) ዕቃው ከሚደርስበት አገር የተሰጠ የታደሠ ንግድ ፈቃድ፤

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ዓለም አቀፍ ተቋማት እና የእርዳታ ድርጅቶች ለተላላፊ ዕቃ የትራንዚት ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን ማቅረብ አለባቸው፤

ሀ) ዋስትና፣

ለ) የማጓጓዣ ሰነድ፣

ሐ) ትራንዚት ዲክለሬሽን (IM8)

7. <u>የሀገር ውስጥ ትራንዚት</u>

1/ ከአንድ የጉምሩክ ጣቢያ ወደ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ ለሚተላለፍ ዕቃ የትራንዚት ፈቃድ ለማግኘት አስመጪው ወይም ወኪሉ የሚከተሉትን ማቅረብ አለበት፤

ሀ) ትራንዚት ዲክለሬሽን (IM8) ፣

ለ) የማጓጓዣ ሰነድ፣

ሐ) ዋስትና፣

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር የሰነድ ማዘጋጃ
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የሰነድ ማዘጋጃ
Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1

8. <u>የወጪ ዕቃ ትራንዚት</u>

ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕቃ የትራንዚት ፈቃድ ለማግኘት ላኪው ወይም ወኪሉ የሚከተሉትን ማቅረብ አለበት፤

ሀ) የወጪ ዕቃ የትራንዚት ዲክለራስዮን (EX8)

ለ) እንደአስፈላጊነቱ የተቆጣጣሪ መ/ቤት ፈቃድ፣

## ምዕራፍ ሁለት

## የጉምሩክ ማሸጊያ እና ልዩ ምልክት

9. <u>የጉምሩክ ማሸጊያ እና ልዩ ምልክት</u>

ኮሚሽኑ ጭነቶችን ለማሸግ የሚጠቀምበት የጉምሩክ ማሸጊያ ወይም ልዩ ምልክት እንደአግባብነቱ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፤

1/ በቀላሉ ለማንበብና ለመለየት የሚቻል፣

2/ ካልተሰበረ ወይም ካልተነሳ በስተቀር ዕቃ ለማውጣትም ሆነ ለማስገባትየማያስችል፣

3/ የኤሌክትሮኒክ ሲል ካልሆነ በስተቀር ለአንድ ጊዜ ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ፣

4/ የጉምሩክ ማሸጊያ ወይም ልዩ ምልክት መሆኑን የሚያሳይ "ETH-CUSTOMS" የሚል የእንግሊዘኛ ጽሑፍ፣ ኮድና ተከታታይ ቁጥር ያለው፣

5/ ለማሸግ ወይም ለመቆለፍ አመቺ የሆነ፣ እና

7/ ለዕቃው ደህንነት አስፈላጊ ነው ብሎ ኮሚሽኑ የሚስነው ሌላ መስፈርት፣

10. <u>መታሸግ ያለባቸው ጭነቶች</u>

1/ ከዚህ በታች የተመለከቱትየትራንዚት ዕቃዎች በጉምሩክ ማሸጊያ መታሸግ አለባቸው፤

ሀ) በኮንቴነር ወይም በዝግ የባቡር ፉርጎ ተጭኖ የሚጓጓዝ ዕቃ፣

ለ) በሸራ ተሸፍኖ የሚጓጓዝ ዕቃ፣

ሐ) ነዳጅ እና የነዳጅ ውጤት፤

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Customs Commission Records & Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የትራንዚት ዕቃ በቀላሉ ሊሰበር ወይም ሊቀሸብ ወይም ሊለወጥ የሚችል ከሆነ እና/ወይም የዓለም አቀፍ ስምምነት የሚከለክል ካልሆነ በስተቀር በጉምሩክ ማሽጊያ መታሸግ ይኖርበታል፡፡

3/ በውጭ አገር የጉምሩክ ሲል የታሸገ ጭነት እሽጉ በቂ ወይም አስተማማኝ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ወይም ጉምሩክ እሽጉን ከፍቶ ከመረመረ ጭነቱ በጉምሩክ ማሽጊያ መታሸግ ይኖርበታል፤

11. <u>የማይታሸጉ ጭነቶች</u>

ከዚህ በታች የተመለከቱት የትራንዚት ዕቃዎች በጉምሩክ ማሽጊያ ሳይታሸጉ ሊጓጓዙ ይችላሉ፡፡

1/ ትልልቅ የፋብሪካ እና የፕሮጀክት ማሽነሪዎች፣

2/ የብረት ጭነቶች፣

3/ ያለኮንቴነር ተጭነው የሚመጡ ተሽከርካሪዎች፣

4/ በውጭ አገርጉምሩክ ማሽጊያ በትክክል የታሸገ ዕቃ፣

5/ በተሽከርካሪ የሚጫን የዕርዳታ እህል፣ ማዳበሪያ እና የድንጋይ ከሰል

6/ ለትራንዚት ቁጥጥር አመቺ የሆኑናበግልጽ የሚታዩ ሌሎች ጭነቶች፤

## ምዕራፍ ሦስት

## የትራንዚት መነሻና መዳረሻ ቦታ፣ መግቢያና መውጫ በር እና መተላለፊያ መሥመር

12. <u>የትራንዚት መነሻ</u>

ወደ ሀገር ለሚገባ ወይም ለተላላፊ ዕቃ የጉምሩክ ትራንዚት መነሻ ቦታ የሚሆኑት፤

ሀ) የጅቡቲ ወደብ፣

ለ) የበርበራ ወደብ፣

ሐ) የሱዳን ወደብ፣ እና

መ) ኮሚሽኑ የሚወስናቸው ሌሎች የጎረቤት ሀገራት ወደቦች ናቸው፡፡

Ethiopian Customs Commission Records & Documentation No.1

## 13. መግቢያ በር

1/ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ለተላላፊ የትራንዚት ዕቃየመግቢያ በር የሚሆኑት፤

ሀ) በጅቡቲ በኩል ለሚገባ ዕቃ - ጋላፊ፣ ታጁራ እና ደወሌ

ለ) በሶማሊያ በኩል ለሚገባ ዕቃ-ቶጎጫሌ፣ ተፈሪ በር፣ ፌረፌር፣ ዱዱብ፣ ቦህ እና ዶሎአዶ፣

ሐ) በሱዳን በኩል ለሚገባ ዕቃ-ሁመራ፣ መተማ የሐንስ፣ አልመሃል፣ በሃምዛ፣ ኩርሙክ እና ጊዘን፣

መ) በደቡብ ሱዳን በኩል ለሚገባ ዕቃ - መተሐር (ቡርቤ)፣ ላሬ (ፓጋግ) እና ራድ

ሠ) በኬንያ በኩል ለሚገባ ዕቃ - ሞያሌ እና ኦሞራቴ፣

ረ/ በኤርትራ በኩል ለሚገባ ዕቃ - ቡሬ፣ ዛላ አምበሳ፣ ራማ እና ሁመራ፣

ሰ) በኮሚሽኑ የሚወሰኑ ሌሎች መግቢያ በሮች ናቸው፡፡

2/ ከሀገር ለሚወጣ ዕቃ ወይም በአገር ውስጥ ከአንዱ የጉምሩክ ጣቢያ ወደ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ ለሚተላለፍ ዕቃ የትራንዚት መነሻ የሚሆኑት፤

ሀ) የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣

ለ) በመግቢያና መውጫ በሮች የሚገኙ የጉምሩክ ጣቢያዎች፣

ሐ) የተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን፣

መ) የኢንዱስትሪ ፓርኮች እና ዞኖች፣

ሠ) በኮሚሽኑ የሚፈቀዱ ሌሎች ቦታዎች ናቸው፡፡

## 14. የትራንዚት መዳረሻ ቦታ

1/ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ወይም በአገር ውስጥ በትራንዚት ለሚተላለፍ ዕቃ የትራንዚት መዳረሻ ቦታ የሚሆኑት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (2) የተዘረዘሩት ቦታዎች ይሆናሉ፡፡

2/ በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩት የጉምሩክ መግቢያ በሮች፣ ከሀገር ለሚወጣ ዕቃ ወይም ለወጪ ተላላፊ ዕቃ የትራንዚት መዳረሻ ቦታዎች ወይም መውጫ በሮች ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

15. <u>የመተላለፊያ መስመሮች</u>

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ወይም ተላለፊ እንዲሁም ከአገር የሚወጣ ዕቃ መተላለፍ ያለበት በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር 1 በተዘረዘሩት የጉምሩክ መተላላፊያ መስመሮች ናቸው፡፡

16. <u>ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች</u>

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ወይም ተላላፊ እንዲሁም ከአገር የሚወጣ ዕቃ ላይ ቁጥጥር የሚያደርጉት የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር 2 ላይ የተዘረዘሩት ይሆናሉ፡፡

17. <u>ክትትልና ቁጥጥር</u>

የትራንዚት ዕቃ የጫነ ማጓጓዣ ከትራንዚት መሥመሩ ውጭ ሆኖ ሲገኝ ወይም ለረጅም ጊዜ በመንገድ ላይ የቆመ እንደሆነ ወይም ለኮሚሽኑ መረጃ ከደረሰ የፓትሮሊንግ ወይም ሌላ የሚመለከተው የሥራ ክፍል ሁኔታውን መከታተልና መቆጣጠር አለበት፡፡

18. <u>ክልከላ</u>

1/ ማንኛውም የትራንዚት ዕቃዎችን የሚያጓጉዝ አጓጓዥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 ላይ ከተዘረዘሩት የተፈቀዱ የመተላላፊያ መስመሮች ውጪ የትራንዚት ዕቃ ማጓጓዝ፣ ማውረድ ወይም መጫን እንዲሁም ማጓጓዣውን ማቆም የለበትም፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም አጓጓዡ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ያጋጠመው እንደሆነ ጉዞ ማቋረጡን በስምንት ሰዓት ውስጥ ለዲክላራሲን አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፤ የዲክላራሲዮን አቅራቢውም በሃያ አራት ውስጥ ሰዓት ለዕቃው መዳረሻ የጉምሩክ ጽ/ቤት ማሳወቅ አለበት፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ጉዞው የተቋረጠበት አጓጓዥ ለጉዞው መቋረጥ ምክንያት የሆነውን ሁኔታ የሚገልጽ ማስረጃ ከሚመለከተው አካልማቅረብ አለበት፤

4/ አጓጓዡ ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ማንኛውንም ሌላ ሰው ወደ ማጓጓዣው እንዲጠጋ መፍቀድ ወይም ማሳፈር፣ የጉምሩክ እሽጎችን መፍታት፣ ማላቀቅ፣ መስበር ወይም መቀየር ወይም እነዚህ ህገወጥ ተግባራት በሌሎች ሰዎች እንዲፈፀሙ ማድረግ የለበትም፤



Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

## <u>የትራንዚት መነሻና መድረሻ ቦታ እና የተፈቀደ ጊዜ</u>

19. <u>የተፈቀደ የጊዜ ገደብ</u>

ማንኛም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ወይም ከሀገር የሚወጣን ዕቃ በተመለከተ አጓጓዥ ከዚህ በታች በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ጉዞውን አጠናቅቆ ለመዳረሻ የጉምሩክ ጽ/ቤት የትራንዚት የመንገድ ወረቀት በማቅረብ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

1/ በጅቡቲ በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ከሀገር ለሚወጣ ዕቃ ፡-

ሀ) ከጋላፊ/ታጁራ - አዳማ/ሞጆ/አዲስ አበባ በሦስት ቀን ውስጥ፣

ለ) ከጋላፊ - ሠመራ በአንድ ቀን ውስጥ፣

ሐ) ከጋላፊ - መቀሌ በሁለት ቀንውስጥ፣

መ) ከጋላፊ - ወረታ በሦስት ቀን ውስጥ፣

ሠ) ከጋላፊ - ኮምቦልቻ በሁለት ቀን ውስጥ፣

ረ) ከጋላፊ - ደብረ-ብርሃን በሦስት ቀን ውስጥ፣

ሰ) ከደወሌ - ደሬዳዋ በአንድ ቀን ውስጥ፣

ሸ) ከደወሌ - ጅግጅጋ በሁለት ቀን ውስጥ፣

ቀ) ከደወሌ - አዳማ/ሞጆ/አዲስ አበባ በሦስት ቀን ውስጥ፣

2/ በሶማሊያ በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ከሀገር ለሚወጣ ዕቃ ፡-

ሀ) ከቶጎጫሌ እና ከተፈሪ በር - ጅግጅጋ እና ድሬዳዋ በአንድ ቀን ውስጥ፣

ለ) ከቶጎጫሌ እና ከተፈሪ በር - አዳማ /ሞጆ/ አዲስ አበባ በሦስት ቀን ውስጥ፣

ሐ) ከፌርፌር፣ ከዱዱብ እና ከቦሀ- ጅግጅጋ እና ድሬዳዋ በአራት ቀን ውስጥ፣

መ) ከፌርፌር፣ ከዱዱብ እና ከቦሀ - አዳማ /ሞጆ/ አዲስ አበባ በስድስት ቀን ውስጥ፣

ሠ) ከዶሎ አዶ - አዳማ /ሞጆ/ አዲስ አበባ በአምስት ቀን ውስጥ፣

Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

3/ በኬንያ በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ከሀገር ለሚወጣ ዕቃ ፡-

ሀ) ከሞያሌ - ሞጆ/አዳማ/አዲስ አበባ በሦስት ቀን ውስጥ፣

ለ) ከሞያሌ - ዶሎ አዶ በሦስት ቀን ውስጥ፣

ሐ) ከሞያሌ - ሀዋሳ በሁለት ቀን ውስጥ፣

መ) ሀዋሳ - ሞጆ /አዳማ/አዲስ አበባ በአንድ ቀን ውስጥ፣

ሠ) ከኦሞራቴ - ሞጆ /አዳማ/ አዲስ አበባ በሦስት ቀን ውስጥ፣

ረ) ከኦሞራቴ - ሀዋሳ በሁለት ቀን ውስጥ፣

4/ በሱዳን በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ከሀገር ለሚወጣ ዕቃ ፡-

ሀ) ከሁመራ- መቀሌ በሁለት ቀን ውስጥ፣

ለ) ከሁመራወይም ከመተማ ዮሐንስ - ወረታ በሁለት ቀን ውስጥ፣

ሐ) ከመተማ ዮሐንስ - ኮምቦልቻ ወይም መቀሌ በሦስት ቀን ውስጥ፣

መ) ከሁመራ ወይም ከመተማ ዮሐንስ - አዲስ አበባ /ሞጆ/ አዳማ በአምስት ቀን ውስጥ፣

ሠ) ከአልምሃል / ከሃምዛ / ከኩርሙክ / ከጊዘን - አዲስ አበባ በሦስት ቀን ውስጥ፣

ረ) ከጎንደር - መተማ ዮሐንስወይምሁመራ በአንድ ቀን ውስጥ፣

ሰ) ከባህር ዳር - መተማ ዮሐንስ ወይም ሁመራ በሁለት ቀን ውስጥ፣

ሸ) ከጎንደር ወይም ከባህር ዳር - አዲስ አበባ በሦስት ቀን ውስጥ፣

ቀ) ከነቀምት - አዲስ አበባ በሁለት ቀን ውስጥ፣

በ) ከነቀምት ወይም ከጅማ - አልምሃል /በሃምዛ /ኩርሙክ /ጊዘን በሁለት ቀን ውስጥ፣

ተ) ከአልመሃል ወይም በሃምዛ - ባህር ዳር በሁለት ቀን ውስጥ፣

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Customs Commission Records & Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenue Records & Documentation No. 2

5/ በደቡብ ሱዳን በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ከሀገር ለሚወጣ ዕቃ ፡-

ሀ) ከመተሃር (ቡርቢ) ወይም ከላሬ (ፓጋግ) ወይም ራድ - አዲስ አበባ በአራት ቀን፣

ለ) ከጅማ ወይም ከነቀምት-መተሃር(ቡርቢ) ወይም ላሬ(ፓጋግ) ወይም ራድ በሁለት ቀን

ሐ) ከጅማ - አዲስ አበባ በሁለት ቀን ውስጥ፣

6/ በኤርትራ በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ከሀገር ለሚወጣ ዕቃ ፡-

ሀ) ከቡሬ- ሠመራ በአንድ ቀን ውስጥ፣

ለ) ከቡሬ - ኮምቦልቻ /ወረታ/ መቀሌ በሁለት ቀን ውስጥ፣

ሐ) ከቡሬ - አዲስ አበባ በሦስት ቀን ውስጥ፣

መ) ከዛላምበሳ ወይም ከራማ - መቀሌ በአንድ ቀን ውስጥ፣

ሠ) ከዛላምበሳ ወይም ከራማ - ወረታ /ኮምቦልቻ/ በሁለት ቀን ውስጥ፣

ረ) ከዛላምበሳ ወይም ከራማ - ሠመራ /ደብረ ብርሃን/ በሦስት ቀን ውስጥ፣

ሰ) ከራማ ወይም ከዛላምበሳ - አዲስ አበባ በአራት ቀን ውስጥ፣

20. <u>አገር አቋርጠው ለሚሄዱ ተላላፊ ዕቃዎች</u>

ኢትዮጵያን አቋርጠው የሚሄዱ ተላላፊ ዕቃዎችየትራንዚት የጊዜ ገደብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 ሥር የተዘረዘሩትን የጊዜ ገደብ የሚያካትት ሆኖ ከመግቢያ በር እስከ አዲስ አበባ ወይም ሌላ ማዕከል ድረስ እና ከአዲስ አበባ ወይም ሌላ ማዕከል እስከ መውጫ በር ድረስ ያለውን ጊዜ ገደብ በመደመር የሚወሰን ይሆናል፡፡

21. <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

1/ የዕቃ መያገር ወይም ማጓጓገር የታሸገበት የጉምሩክ ማሸጊያ የተፈታ ወይም የተነሳ ወይም የተቀየረ ወይም የተበጠሰ እንደሆነ በመግቢያ በር ወይም በመተላለፊያ መስመር የሚገኝ የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ምትክ/ተጨማሪ ማሸጊያ ያደርጋል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው ቢኖርም የተፈታውን ወይም የተበጠሰውን ወይም የተነሳውን ማሸግያ መተካት ሳይቻል ሲቀር ወይም በስካኒንግ ማሽን ፍተሻ መሠረት የጎላ የእቃ ልዩነት መኖሩን የሚያመለክት መረጃ ሲገኝ ወይም ቅ/ጽ/ቤቱ ወይም

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን *1 * Ethiopian Customs Commission Records-Documentation No.1
Ministry of Revenue Records & Documentation No. 2

ጣቢያው በደረሰው መረጃ መሠረት እጀባ እንዲደረግ ሲወሰን በቅ/ጽ/ቤቱ ወይም በጣቢያው የጉምሩክ ማሸጊያ በማሸግ ታጅቦ ወደ መዳረሻ ጣቢያው እንዲጓጓዝ ይደረጋል፤

3/ ከተላላፊ ዕቃ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ለሚታጀብ ዕቃ የሚወጣወጪ ዕቃው በሚያሳጅበው የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ የሚሸፈን ይሆናል፤

4/ የመዳረሻ ጣቢያዎች በዚህ መመሪያ መሠረት ታጅበው የመጡ ዕቃዎች የደረሱበትን ሁኔታ እና በፍተሻ የሚደረስበት ግኝት /ልዩነት/ አሳጅቦ ለላከው ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ በጽሑፍ የማሳወቅ፤

22. <u>ለህዝብ ስለማሳወቅ</u>

ኮሚሽኑ በዚህ መመሪያ መሠረት የተወሰኑ የመግቢያና የመውጫ በሮች፣ ማቋረጫዎች እንዲሁም የመተላለፊያ መስመሮች በአዋጁ አንቀጽ 140 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት በህዝብ ማስታወቂያ ይገልጻል፡፡

23. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነትየማይኖራቸው ሕጎች</u>

1/ የጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 117/2008 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮች እና የአሰራሮች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

24. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

የካ;ቲት --- ቀን 2012 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

አዳነች አቤቤ
የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን *1 Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1

አባሪ አንድ - የትራንዚት መተላለፊያ መሥመሮች

1/ በጅቡቲ በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ከአገር ለሚወጣ ወይም አገር አቋርጦ ለሚያልፍ የትራንዚት ዕቃ የመተላለፊያ መሥመር የሚሆነው፡-

ሀ) ጋላፊ--->ሰርዶሚዳ--->ሠመራ--->ሚሌ--->አዋሽ--->አዳማ--->ሞጆ--->አዲስ አበባ

ለ) ጋላፊ --->ሰርዶሚዳ--->አፍዴራ---->መቀሌ

ሐ) ጋላፊ--->ሰርዶሚዳ--->ሠመራ---->ሚሌ--->ጭፍራ--->ወልዲያ--->ወረታ/መቀሌ

መ) ጋላፊ--->ሰርዶሚዳ--->ሠመራ--->ሚሌ--->ባቲ--->ኮምቦልቻ--->ደብረብርሃን

ሠ) ጋላፊ--->ሰርዶሚዳ--->ሠመራ--->ሚሌ--->አዋሽ--->አንኮበር--->ደብረብርሃን

ረ) ደወሌ--->ቢዮቆቦቤ--->ድሬደዋ>ሐረር--->ጅግጅጋ

2/ በሱማሊያ በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ከአገር ለሚወጣ ወይም አገር አቋርጦ ለሚያልፍ የትራንዚት ዕቃ የመተላለፊያ መሥመር የሚሆነው፡-

ሀ) ቶጎጫሌ /ተፈሪ በር /ፌርፌር /ዱዱብ /ቦሀ--->ጅግጅጋ--->ሐረር--->ድሬዳዋ (ሚኤሶ--->አዋሽ--->አዳማ--->ሞጆ--->አዲስ አበባ)

ለ) ዶሎ አዶ--->ነገሌ ቦረና--->ሀዋሳ--->ሻሸመኔ--->ዝዋይ--->ሞጆ--->አ/አ

3/ በኬንያ በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ከአገር ለሚወጣ ወይም አገር አቋርጦ ለሚያልፍ የትራንዚት ዕቃ የመተላለፊያ መሥመር የሚሆነው፡-

ሀ) ሞያሌ--->ያቤሎ--->ቡሌ ሆራ--->ዲላ--->ሀዋሳ--->ሻሸመኔ--->ዝዋይ--->ሞጆ--->አ/አ

ለ) ኦሞራቴ--->አርባምንጭ--->ወላይታሶዶ--->ሀዋሳ/ቡታጅራ--->አ/አ (ዝዋይ>ሞጆ>አ/አ)

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን *1
Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1
Ministry of Re... Records & Documentation No. 2

4/ በሱዳን በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ከአገር ለሚወጣ ወይም አገር አቋርጦ ለሚያልፍ የትራንዚት ዕቃ የመተላለፊያ መሥመር የሚሆነው፡-

ሀ) ሁመራ--->ሽሬ--->መቀሌ/ጎንደር--->ወረታ--->ባህር ዳር--->ደ/ማርቆስ--->አ/አ

ለ) መተማ--->ጎንደር--->ወረታ--->ባ/ዳር--->ደ/ማርቆስ--->አ/አ(ጎንደር-->ሽሬ-->መቀሌ)

ሐ) ጊዘን / ኩምሩክ--->አሶሳ--->ነቀምት--->አምቦ--->አ/አ (ነቀምት--->ጅማ)

መ) አልመሃል--->በሃምዛ--->ቻግኒ--->እንጂባራ--->ባህርዳር/ወረታ (ደ/ማርቆስ--->አ/አ)

5/ በደቡብ ሱዳን በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ከአገር ለሚወጣ ወይም አገር አቋርጦ ለሚያልፍ የትራንዚት ዕቃ የመተላለፊያ መሥመር የሚሆነው፡-

ሀ) መተሃር /ቡርቤ/--->ጋምቤላ--->በደሌ--->ጅማ--->ወልቂጤ--->አዲስ አበባ

ለ) ላሬ /ፓጋግ/--->ጋምቤላ--->በደሌ--->ጅማ--->ወልቂጤ--->አዲስ አበባ

ሐ) ራድ--->ዲማ--->በበቃ--->ሚዛን--->ቦንጋ(ቴፒ-->ማሻ-->ጎሬ-->መቱ--->በደሌ)-->ጅማ--->ወልቂጤ--->አዲስ አበባ

6/ በኤርትራ በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ከአገር ለሚወጣ ወይም አገር አቋርጦ ለሚያልፍ የትራንዚት ዕቃ የመተላለፊያ መሥመር የሚሆነው፡-

ሀ) ቡሬ--->ሰርዶ ሚዳ--->ሠመራ--->ሚሌ--->አዋሽ--->አዳማ--->ሞጆ--->አዲስ አበባ

ለ) ቡሬ---ሰመራ---ሚሌ-----ባቲ---ኮምቦልቻ--->ደብረ ብርሃን

ሐ) ዛላአንበሳ--->ዓዲ ግራት--->መቀሌ--->ወልዲያ--->ኮምቦልቻ--->ደብረ ብርሃን--->አ/አ

መ) ራማ--->ዓድዋ--->ተምቤን--->መቀሌ--->ወልዲያ--->ኮምቦልቻ--->ደ/ብርሃን--->አ/አ

ሠ) ሁመራ--->ጎንደር--->ወረታ--->ባህር ዳር--->ደብረ ማርቆስ--->አዲስ አበባ

ረ) ሁመራ--->ሽሬ--->መቀሌ

7/ በባቡር ተጭነው ለሚጓጓዙ ዕቃዎች ባቡር የሚያልፈባቸው መስመሮች የትራንዚት መተላለፊያ መስመር ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

| አባሪ ሁለት - የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች እና በሥራቸው የሚገኙ ጣቢዎች | | |
|---|---|---|
| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ ጽ/ቤት | መቅረጫ / መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 1 | ጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት | ሰርዶ ሜዳ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 2 | | ቡሬ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 3 | | ታጁራ (ሞደዲና / ፓራዲዞ) ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 4 | አዋሽ ቅ/ጽ/ቤት | ሠመራ ጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ |
| 5 | | አሳኢታ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 6 | | ሚሌ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 7 | | አልበረኮቴ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 8 | ኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት | ወልዲያ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 9 | አዳማ ቅ/ጽ/ቤት | |
| 10 | ሞጆ ቅ/ጽ/ቤት | |
| 11 | አዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት | ቱሉ ዲሚቱ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 12 | | አቃቂ ቃሊቲ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 13 | ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት | ደወሌ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 14 | | ቢዮቆቤ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 15 | | ዱሬ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 16 | | ደንበል ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 17 | | ሐረር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 18 | ጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት | ቶጎጫሌ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 19 | | ተፈሪ በር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 20 | | ሀርቲ ሼክ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 21 | | ሀርሺን ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 22 | | ቦምባስ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 23 | | ጭናቅሰን ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 24 | | ዳሮር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 25 | | ጋሻሞ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 26 | | ቦሀ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 27 | | ጎዴ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 28 | | ዱዱብ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 29 | | ቀላፎ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 30 | | ፌርፌር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 31 | | ቀብሪ ደሃር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 32 | | ገላዲ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 33 | | ዋርዴር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 34 | ሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት | ሞያሌ መውጫ በር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 35 | | ያቤሎ የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 36 | | ቡሌ ሆራ የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 37 | | ዶሎ ኦዶ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 38 | | ነጌሌ ቦረና ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |

Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

| | | |
|---|---|---|
| 39 | | ገናሌ ድልድይ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 40 | | መልዩ ሜዳ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 41 | | ገናሌ ድልድይ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 42 | | ዲላ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 43 | | ዳዬ ማዞሪያ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 44 | | ጊኒር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 45 | | ዶሎ ሰብሮ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 46 | ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት | ኦዳ ሮባ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 47 | | አዳባ (ወሻ) ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 48 | | ሻሸመኔ (ኩየራ) ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 49 | | ኮንሶ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 50 | | አሞራቴ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 51 | | ጊዞን ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 52 | | ኩርሙክ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 53 | | ባሃምዛ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 54 | | አልመሃል ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 55 | | አሶሳ ጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ |
| 56 | ጅማ ቅ/ጽ/ቤት | መተሐር (ቡርቤ) ጉምሩክ መቆ/ጣቢያ |
| 57 | | ላሬ (ፖጋግ) ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 58 | | ጋምቤላ ጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ |
| 59 | | ጌዶ የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 60 | | ወልቂጤ/ጊቤ የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 61 | | ራድ የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 62 | | መተማ ዮሐንስ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 63 | | ሰረባ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 64 | ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት | ጎንደር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 65 | | ምድረ-ገነት (አብደራፊ) የጉምሩክ መቆ/ጣቢያ |
| 66 | | ውሻ ጥርስ የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 67 | | ሳንጃ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 68 | | ሉግዲ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 69 | | ዲማ ጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ |
| 70 | | ሁመራ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 71 | | ዛላምበሳ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 72 | | ራማ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 73 | መቀሌ ቅ/ጽ/ቤት | አላማጣ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 74 | | ዲማ ጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ |
| 75 | | ማይካድራ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 76 | | ዓዲ-ረመጽ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 77 | | መሆኒ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| 78 | | ማይተመን ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ |
| | በባቡር ጣቢያዎች የሚገኙ ሁሉም የጉምሩክ መቅረጫ/መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች | |

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2
Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1